# ኪ ዳ ና ች ን
# KIDANACH'N

ልዩ ዕትም
Special Edition

መስከረም ፩ ቀን፥ ፳፻ (፪ሺ) ዓ. ም.
Meskerem 1, 2000 A.D
(September 12, 2007)

**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥**
**ኢትዮጵያውያንም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳትና**
**የ“ኢትዮጵያ” እና “የኢትዮጵያውያን” የኾነውንም ኹሉ ለመጠበቅ፥ ለማሳወቅም፡**
**በ“ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት” እየተዘጋጀ የሚወጣ ዕትም፡፡**

**Published by "Ethiopia: The Kingdom of God Services"**
**to reveal the truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God**
**and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God;**
**and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.**

---

# የ፳፻ (፪ሺ) ዓመተ ምሕረት
# ቀን መቁጠሪያ
# 2000 (2007–2008 **Gregorian**) **Calendar**

---

**አዘጋጅ፡- ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ**



ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ኢየሱስ ክርስቶስ
ካህኑ ለዓለም፥ ንጉሠ ጽዮን
<u>ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u>

The Conquering Lion of the Tribe of Judah
Jesus Christ
Eternal Priest, King of Zion and
King of Kings of Ethiopia

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
ድንግል ማርያም
እሙ ወእምነ፥ ንግሥተ ጽዮን
<u>ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u>

Ethiopia stretches out Her Hands to God
The Virgin Mary
Mother of God and Our Holy Mother
Queen of Zion and Ethiopia

# ልዑል እግዚአብሔር፡
# ከዘመነ ሉቃስ ወደዘመነ ዮሐንስ አሸጋግሮ፡

# የ፯ሺ፭፲ኛውን ዓመት
# የነጻነት ህልውና በዓላችንን፥

# የ፪ሺኛውን ዓመት
# የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን
# እና
# የእመቤታችን ድንግል ማርያምን
# የልደታት በዓል ለማክበር ለበቃንበት፡

# ለአዲሱ የ፳፲ (፪ሺ) ዓመተ ምሕረት፡ እንኳን አደረሰን!

# ስለቀን መቁጠሪያው መግለጫ

፩ኛ፡- ይህ የቀን መቍጠሪያ የተዘጋጀው፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በሚለው፡ በ፲፱፻፺፫ ዓ. ም. በታተመው መጽሐፍ ውስጥ የተገለጹትንና አግባብነት ያላቸውን ሐተታዎች መሠረት በማድረግ ነው።

፪ኛ፡- "በዘንዜከር" በተባለው፡ የየዕለቱ፡ የጸሎት መግቢያ፡ ለመዓልቱና ለሌሊቱ ቅመራ፡ መነሻ ኾኖ፡ ከሌሎቹ ቁጥሮች ጋር የሚደመረው፡ የ፳፻፩ ዓ. ም. ዓበቅቴ፡ ፳፫ (ሃያ ሦስት)፥ መጥቅዑ፡ ፯ (ሰባት) ነው።

፫ኛ፡- በቀን መቁጠሪያው ሠንጠረዥ ውስጥ፡ በስም ብቻ የተጠቀሱት ቅዱሳን ጻድቃንና ሰማዕታት፡ <u>ዕረፍታቸውን</u>፥ የአኀዞቹ  የተለያዩት ቀለማት ደግሞ፡ የሚከተሉትን አብነቶች ያመለክታሉ።

(ሀ) ቀዩ፡ ሰንበተ ክርስቲያንን፥ ዓበይት በዓላትንና ተከታታዮቹን የሓሜት ዕለታት፥

(ለ) አረንጓዴው፡ ቀዳሚት ሰንበትንና ንዑሳን በዓላትን፥

(ሐ) ሰማያዊው፡ የሰባቱን አጽዋማት ቀኖች፡ ረቡዕንና ዓርብን ጭምር ያሳያሉ።

፬ኛ፡- መስከረም ፩ ቀን፡ አሮጌ የኾነውን ኹሉ ጥለን፥ ከየኹለንተናችን፡ በንስሓ አስወግደንና በመንፈስ ቅዱስ ታድሰን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም በመወለዱ፡ የተገኘውን፡ ዘለዓለማዊዉን የምሕረት ዘመን፥ የክብር ልብስና የሕይወት አክሊል፡ እንደአዲስ ተሸላሚዎች፡ ተቀብለን የምንጐናጸፍባትና የምንቀዳጅባት ዕለት ስለኾነች፥ ከዚህም ጋር፡ ለጌታችንና ለእመቤታችን የልደት በዓላት አክብሮት፡ ሥጋችንንና ነፍሳችንን፥ መንፈሳችንንም፡ በሥጋ ወደሙ ቀድሰን ለማብቃት፡ ከአሮጌው፡ ወደአዲሱ ዓመት የምንሸጋገርባትን ጳጕሜን፡ እንደጾመ ገሃድና ንዑስ ሱባኤ አድርገን፡ በጸሎት እናሳልፋታለን።

፭ኛ፡- በቀን መቍጠሪያው የየወሩ ሠንጠረዥ ግርጌ፡ ለየወሩ የተመደቡት ምንባቦች ተመልክተዋል። እነዚህም የተዘጋጁት፡ በሳምንቱ የሥራ ቀኖች፡ በየዕለቱ፡ ለጧትና ለማታ፡ እጅግ ቢያንስ፡ ኹለት ምዕራፎችን፥ እንዲሁም፡ በየሳምንቱ የቅዳሜና እሑድ ዕለታት፥ በሌሎቹም የበዓላትና የዕረፍት ጊዜያት፡ በተቻለ መጠን፡ ምዕራፎቹን ጨማምሮ በማንበብ ለመጨረስ እንደሚቻል በመገመት ነው። መዝሙረ ዳዊት፡ በየቀኑ፡ በጸሎት መልክ ስለሚደገም፡ በምንባቡ ውስጥ አልታከለም።

፮ኛ፡- ጾሙና ጸሎቱ፥ የሱባኤው ጭምር፥ ምንባቡም፡ በግል፥ በቤተሰብ፥ ወይም በኅብረት በመሰባሰብ ሊካኼድ ይቻላል።

፯ኛ፡- ይህን የቀን መቍጠሪያ፥ ደግሞም፡ በቅርቡ፥ "ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት" በሚል፡ አዲስ ተከታታይ ርእስ ሥር፡ "አንደኛ መጽሓፍ"፥ "ኹለተኛ መጽሓፍ" እና "ሦስተኛ መጽሓፍ" ተብለው፥ እንዲሁም፡ ቀደም ብለው፡ "ኢትዮጵያዊው፥ በማንነቱ ፍለጋ!"፥ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" እና **Ethiopia: The Classic Case** በሚሉ አርእስት፡ ታትመው የወጡትንና እየተሠራጩ ያሉትን፥ ሌሎችንም፡ ወደፊት እየታተሙ የሚወጡትን ዕትሞችና መጻሕፍት ለማግኘት፡ የጎዋ ሰሌዳችንን መጎብኘት፥ እንዲሁም፡ ከዚህ በታች በተመለከቱት፡ ባሳታሚው አድራሻዎችና የመገናኛ መስመሮች፡ መጠየቅና መጠቀም ይቻላል።


አሳታሚ እና አከፋፋይ
Publisher & Distributor
**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት።**
**Ethiopia: The Kingdom of God Services**
መልእክት ሣጥን ቁጥር ፰፻፲፪ P. O. Box 812
ስልክና ዕምነቅ ቁ. ፲፮-፲፰-፹፭ እና ፳-00-፹፭ Tel. & Fax. 16-18-85 & 20-00-85
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ። Addis Abeba, ETHIOPIA
ወይም or
**P. O. Box 43262 ~ Washington, DC 20010-9262 ~ USA.**
**Tel.: 301-587-8074 ~ Fax.: 301-587-1971**
Email: ekogyesus@aol.com
Web Site: www.ethkogserv.org


\+ \+ \+

# ፳፻ ዓመተ ምሕረት ወርኀ መስከረም ዘመነ ዮሓንስ ወንጌላዊ

2000 Era of Mercy. Month of Meskerem (Sept.-Oct., 2007). Year of John the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | ፩ 12<br>የኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም ልደታት፡ የኢትዮጵያ ነጻነት፤ ኪዳነ አዳምና ሔዋን፤ ራጉኤል ሊቀ መላእክት፤ ቅዱስ ዮሓንስ መጥምቅ፤ በርተሎሜዎስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ:: | ፪ 13<br>ዮሓንስ መጥምቅ፤ | ፫ 14<br>አባ አንበስ ኢትዮጵያዊ | ፬ 15 |
| ፭ 16<br>በሄሮድስ የተፈጁት ሕፃናት፤ አጼ ንብለ ድንግል፡ የአሕመድ ግራኝን ወረራ፡ በሃይማኖት ጽናት ተቋቁሞ የተጋደለ:: | ፮ 17<br>ኢሳይያስ ነቢይ | ፯ 18<br>ኢትዮጵያዊቷ ኤልሣቤጥ፡ የመጥ ምቁ ዮሓንስ እናት:: መናኔ መንግሥት አጼ ተክለ ሃይማኖት ዙፋኑን ትቶ፡ ወደገዳም የገባ:: | ፰ 19<br>ግዝረተ ኢየሱስ | ፱ 20 | ፲ 21<br>አጼ መስቀል:: (ግማደ መስቀሉ በ፲፭ኛው፻ዓመት በ፩ኛአጼ ዳዊት ወደኢትዮጵያ ስለገባ "አጼ መስቀል" ተባለ) | ፲፩ 22<br>አጼ በካፋ፡ ስመ ጥሩው ምሁር መሪ:: |
| ፲፪ 23<br>ስለንስጥሮስ ኑፋቄ የ፪፻ ሊቃውንት ጉባኤ በኤፌሶን | ፲፫ 24 | ፲፬ 25 | ፲፭ 26 | ፲፮ 27<br>ኪዳነ ኖኅ::<br>ደመራ፡ (በመስቀል ዋዜ ማ ማታ፡ በችቦ እሳት በሚነድ ቋሚ ላይ ለጋ ዛፍ መደመር) | ፲፯ 28<br>በዓለ መስቀል<br>ኢየሱስ ክርስቶስ የተሠዋበት እውነተኛው መስቀል የተገኘበት:: | ፲፰ 29<br>አባ ኤዎስጣቴዎስ ኢትዮጵያዊ፡ ስለቅዳሜ፡ ቀዳሜ ሰንበትነት የተከራከረ:: |
| ፲፱ 30 | ፳ 1 | ፳፩ 2<br>የቅድስት ድንግል ማርያም ዕርገት፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ዜና መስቀል በግሼን የሚነገርበት | ፳፪ 3 | ፳፫ 4 | ፳፬ 5<br>ኪዳነ መልከ ጼዴቅ | ፳፭ 6<br>ዮናስ ነቢይ፤ የክረምት ወራት ማብቂያ |
| ፳፮ 7<br>የጽጌ ወራት መግቢያ፤<br>የጽጌ ማኅሌት | ፳፯ 8 | ፳፰ 9<br>ኪዳነ አብርሃም፤ | ፳፱ 10 | ፴ 11 | ማስታወሻ:- | |

*"ወንዝም፡ ገነትን ያጠጣ ዘንድ፡ ከዔዶም እየወጣ ይፈስስ ነበር፤ ከዚያም ለአራት ወገን ይከፈል ነበር::  ...የወንዙ ኹለተኛ ወገን ስም፡ ግዮን ነው፤ እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ኹሉ ይከብባል::  ...እግዚአብሔር አምላክም፡ ሰውን ወስዶ፡ ያበጃትም፥ ይጠብቃትም ዘንድ፡ በዔዶም ገነት አኖረው::"* ዘፍጥ. ፪፥ ፰-፲፯::

| | |
|---|---|
| የመስከረም ወር ምንባብ:- | ኦሪት ዘፍጥረት እና መጽሓፈ ጥበብ:: |

# ፳፻ ዓመተ ምሕረት ወርኀ ጥቅምት ዘመነ ዮሐንስ ወንጌላዊ

2000 Era of Mercy. Month of T'q'mt (Oct.-Nov., 2007). Year of John the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | | | ፩ 12 | ፪ አባ 13<br>ሕርያቆስ: የቅዳሴ ማርያም ደራሲ |
| ፫ 14<br>የጽጌ ማኅሌት | ፬ 15<br>አብርሃ ወአጽብሓ: ክርስትናን በኢትዮጵያ ያስፋፉ ወንድማማች ነገሥት:: | ፭ 16 | ፮ 17<br>ሓና ነቢይት: የሳሙኤል እናት፤ አባ ጸንጠሌዎን: ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ:: | ፯ 18 | ፰ 19 | ፱ አጼ ዳዊት: 20<br>የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ግማደ መስቀል ከኢየሩ ሳሌም ያስመጣና 'ዓባ ይን እገድባለሁ' እያለ: በዚያ አካባቢ የሚኖሩ ክርስቲያኖችን: ከእስላ ሞች ጥቃት ያዳነ:: |
| ፲ ኢየሱስ 21<br>ክርስቶስ በ፵ ቀኑ በእናቱ እቅፍ ቤተ መቅደስ የገባበት፤ በዓለ ስምዖን፤ ሓና ነቢይት፤ አጼ ፋሲል ካቶሊክነትን ተቃ ውሞ: ተዋሕዶ ሃይ ማኖትን ያጸና::<br>የጽጌ ማኅሌት | ፲፩ 22<br>የሕፃኑ ኢየሱስና የቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ስደት መታሰቢያና የስደት ጾም መግቢያ | ፲፪ 23<br>ወንጌላዊው ማቴዎስ: ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ፤ ቅዱስ ድሜጥሮስ: የቀንና የዘመን አቈጣጠርን ያስተካከለ:: | ፲፫ 24 | ፲፬ 25<br>ኢትዮጵያዊዉን ጃንደረባ አቤሜሌክን ያጠመቀው ፊልጶስ ሓዋርያ፤ አባ ዘሚካኤል አቡነ አረጋዊ: ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ፤ ገብረ ክርስቶስ:: | ፲፭ 26 | ፲፮ 27 |
| ፲፯ 28<br>እስጢፋኖስ: ቀዳሚው ሰማዕት: የሹመቱ መታሰቢያ:: ዲዮስቆሮስ ሊቀ ካህናት ዘግብፅ: የተዋሕዶ ሃይማኖት ተጋዳይ::<br>የጽጌ ማኅሌት | ፲፰ 29 | ፲፱ 30<br>አጼ ይምራሕ፤ የመጀመሪያዎቹን እስላም ስደተኞች በኢትዮጵያ አስተ ናግዶ የሸኘውና እነርሱ "ነጋሽ" የሚሉት ክርስቲ ያኑ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ:: | ፳ 31 | ፳፩ 1 | ፳፪ 2<br>ወንጌላዊው ሉቃስ | ፳፫ 3 |
| ፳፬ 4<br>የጽጌ ማኅሌት | ፳፭ 5 | ፳፮ 6 | ፳፯ 7<br>መድኃኔ ዓለም | ፳፰ 8<br>አማኑኤል፤ አባ ይምዓታ: ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ:: | ፳፱ 9 | ፴ 10 |

*"እግዚአብሔር: ኖኅን አለው:-'የፈጠርሁትን ፍጥረት ኹሉ: ከሰው እስከእንስሳ÷ ከተንቀሳቃሽ እስከ ሰማይ ወፍም ድረስ: ከምድር ገጽ አጠፋለሁና: አንተ: ቤተሰቦችህን ኹሉ ይዘህ: ወደመርከብ ግባ! በዚህ ትውልድ መካከል: በፊቴ: የእውነት ሰው ኾነህ አግኝቼሃለሁና!' ኖኅም: እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ::...እግዚአብሔርም: በስተኋላው ዘጋበት:: የጥፋት ውኃም: በምድር ላይ: አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ዘነበ፤ ውኃውም በዛ፤ መርከቢቱንም አነሣ፤ እርሷም: በውኃው ላይ ተንሳፈፈች!"* የጥምቀት ምሳሌ ለኾነው: ለመጀመሪያው ሃይማኖታዊ ጕዞ: ቀይ ባሕርን አቋርጣ: አራራት ላይ ለማረፍ: ከኢትዮጵያ ተነሣች:: ዘፍጥ. ፯÷ ፩-፲፯::

| | |
|---|---|
| የጥቅምት ወር ምንባብ:- | መጽሓፈ ኢዮብ እና መጽሓፈ ሲራክ:: |

# ፳፻ ዓመተ ምሕረት ወርኀ ኅዳር ዘመነ ዮሓንስ ወንጌላዊ

2000 Era of Mercy. Month of H'dar (Nov.-Dec., 2007). Year of` John the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 11<br>አጼ ነአኵቶ ለአብ መንግሥቱን፡ በኢትዮጵያዊው የመልከ ጼዴቅ ሥርዓት የመራና ያስተዳደረ:: የጽጌ ማኅሌት ፍጻሜ:: | ፪ 12 | ፫ 13 | ፬ 14 | ፭ 15<br>ለንጊኖስ፡ የተሰቀለ ጌታን፡ ጎኑን በጦር የወጋና ኋላ አምኖ፡ በሰማዕ ትነት የተጋደለ:: የስደት ጾም ማብቂያ | ፮ 16<br>ቍስቋም፤ የሕፃኑ ኢየሱስ እና የቅድስት እናቱ የስደት መታሰቢያ በዓል | ፯ 17 |
| ፰ 18<br>የእግዚአብሔርን መንበር የሚሸከሙ አራቱ እንስሶች:: | ፱ 19<br>ስለአርዮስ ኑፋቄ የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ጉባኤ በኒቅያ:: | ፲ 20 | ፲፩ 21<br>ቅድስት ሐና ኢትዮጵያዊት፡ የድንግል ማርያም እናት:: | ፲፪ 22<br>ሚካኤል ሊቀ መላእክት፤ አጼ በእደ ማርያም ሃይማኖታዊው ተጋዳይ:: | ፲፫ 23<br>አእላፍ መላእክት | ፲፬ 24<br>በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. በደርግ የዓመፅና የክህደት ዘመን፡ የኢትዮጵያውያን እልቂት መነሻ |
| ፲፭ 25 | ፲፮ 26<br>የጾመ ነቢያት መግቢያ | ፲፯ 27<br>አዲስ አበባ በ፲፰፻፸፱ ዓ.ም. የተቈረቈረችበት | ፲፰ 28<br>ፊልጶስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ | ፲፱ 29 | ፳ 30 | ፳፩ 1<br>ኪዳነ ሙሴ፤ ማርያም ጽዮን፤ ማክዳ ንግሥትና ልጇ ምኒልክ:: |
| ፳፪ 2 | ፳፫ 3<br>ቆርነሌዎስ ጻድቅ (የሓዋ. ምዕ. ፲) | ፳፬ 4 | ፳፭ 5<br>መርቆሬዎስ ሰማዕት | ፳፮ 6<br>፳፬ቱ ካህናተ ሰማይ፤ በናግራን (የመን) የኢትዮጵያውያን ሰማዕታት፤ በዚያ የአጼ ካሌብ ድል፤ ኢየሱስ ሞዐ ዘሓይቅ:: | ፳፯ 7<br>አባ ሊቃኖስ ኢትዮጵያዊ ዘደብረ ቍንጽል | ፳፰ 8<br>አባ ሊቃኖስ፡ ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ |
| ፳፱ 9<br>የሊቀ ሓዋርያት ጴጥሮስ ደቀ መዝሙር ቀሌምንጦስና የሰማዕታት መጨረሻ ጴጥሮስ | ፴ አጼ 10<br>ገብረመስቀል፤ በዘመኑ፡ የቅዱስ ያሬድ ሙያና የ፱ቱ ቅዱሳን ዜና የገነነበት፤ የጾመ ነቢያት ማብቂያ:: | ማስታወሻ፡- | | | | |

*"...የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን የኾነው መልከ ጼዴቅ፡ የኅብስተ አኰቴትና የጽዋዓ በረከት ቁርባንን አዘጋጅቶ፡ አብራም፡ ጠላቶቹን ነገሥታት ወግቶ ሲመለስ፡ 'አብራም፡ ሰማይንና ምድርን ለሚገዛ፡ ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው' ብሎ ባረከው፤ አብራምም፡ ከኹሉ ሀብቱ፡ አሥራትን፡ ለመልከ ጼዴቅ ሰጠው::"* የእሥራኤላውያን አባት የኾነውን፡ አብርሃምን፡ ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ያበቃው፡ የኢትዮጵያውያን አባት የኾነው፡ የኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ ቡራኬ መኾኑን ማስተዋል ነው:: ዘፍጥ. ፲፬፥ ፲፯-፳::

| | |
|---|---|
| የኅዳር ወር ምንባብ፡- | ኦሪት ዘፀአት እና ትንቢተ ኤርምያስ:: |

# ፳፻ ዓመተ ምሕረት ወርኀ ታኅሣሥ ዘመነ ዮሐንስ ወንጌላዊ

2000 Era of Mercy. Month of Tah'sas (Dec., 2007-Jan, 2008). Year of John the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | ፩ 11<br>ዕለተ ትስብእት: ኢየሱስ ክርስቶስ የተፀነሰበት፤ ብሥራተ ገብርኤል፤ ኤልያስ ነቢይ፤ ቤትሳባ ኢትዮጵ ያዊት: የሰሎሞን እናት፤ | ፪ 12<br>የጾመ ማርያም መግቢያ:: | ፫ 13<br>ሕጻን ማርያም በስዕለት ለቤተ መቅደስ የተሰጠች በት፤ ፋኑኤል ሊቀ መላእክት፤ ዳግማዊ አጼ ምኒልክ፤ ሀብተ ጊዮርጊስ አባ መላ:: | ፬ 14<br>እንድርያስ: ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ | ፭ 15 |
| ፮ 16<br>በ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. በፋሺስት ጣልያን: በሰማዕትነት የተሰየፉት የአዲስ ዓለም ማርያም ካህናት | ፯ 17<br>ፅንሰታ ለማርያም (ድንግል ማርያም የተፀነሰችበት) | ፰ 18<br>ኢትዮጵያዊው አባ ኪሮስ | ፱ 19<br>አባ በአሚን፤ ኢትዮጵያዊ | ፲ 20<br>በወሎ: ደብረ እግዚአብሔርና የሓይቅ መካነ እስጢፋኖስ: በአሕመድ ግራኝ ጦር የተበዘበዙበት | ፲፩ 21 | ፲፪ 22<br>ኢትዮጵያዊው አባ ሳሙኤል: የዋልድባው |
| ፲፫ 23<br>ስብከት | ፲፬ 24<br>በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. የፋሺስት ጣል ያን አየር ኃይል በኢትዮጵያ ላይ የመርዝ ጢስን ማዝነብ የጀመረበት | ፲፭ 25 | ፲፮ 26 | ፲፯ 27 | ፲፰ 28<br>በአኵሱሙ ሊቀ ካህናት እንበረም ተልኮ የግብፅን ጵጵስና አገዛዝ ወደኢት ዮጵያ ያመጣ አባ ሰላማ | ፲፱ 29<br>ቅዱስ ገብርኤል ፫ቱ ደቂቅን ከባቢሎን እሳት ያዳነበት |
| ፳ 30<br>ብርሃን | ፳፩ 31 | ፳፪ 1 | ፳፫ 2<br>ኪዳነ ዳዊት | ፳፬ 3<br>የእቲሳው እጨጌ ተክለ ሃይማኖት ልደት | ፳፭ 4<br>የጽጌ ወራት ማብቂያ | ፳፮ 5<br>የበጋ ወራት መግቢያ |
| ፳፯ 6<br>ኖላዊ<br>አጼ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ | ፳፰ 7<br>አማኑኤል | ፳፱ 8<br>በዓለ ወልድ | ፴ 9 | ማስታወሻ:- | | |

*ኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ ከባረከው በኋላ: እግዚአብሔር ተገልጦለት: "እኔ ኤልሻዳይ ነኝ! በፊቴ ተመላለስ! ፍጹምም ኹን! ቃል ኪዳኔን: በእኔና በአንተ መካከል አደርጋለሁ! እጅግም አበዛሃለሁ! ...ከዛሬ ጀምሮም: እንግዴህ: ስምህ 'አብራም' ተብሎ አይጠራ! ነገር ግን ስምህ: 'አብርሃም' ይኾናል፤ ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና!" ያለው: ይህ የሃይማኖትና የምግባር ሰው: ከተገረዘና ሣራ ከሞተች በኋላ: ኢትዮጵያዊቷን ኬጡራን: በሚስትነት አግብቶ: ልጆ ችን መውለዱ: ለኢትዮጵያዊነት አንዱ አብነት ኾኗል:: ዘፍጥ. ፲፯፤ ፳፤ ፳፭::*

| | |
|---|---|
| የታኅሣሥ ወር ምንባብ:- | መጽሓፈ ሳሙኤልና ትንቢተ ሕዝቅኤል:: |

# ፳፻ ዓመተ ምሕረት ወርኀ ጥር ዘመነ ዮሓንስ ወንጌላዊ

2000 Era of Mercy. Month of Tt'rr (Jan.-Feb., 2008). Year of John the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | | ፩ 10<br>እስጢፋኖስ:<br>እንደጌታው:<br>ለእውነት<br>በይፋ መስክሮ<br>የተሠዋ ቀናዒ<br>አገልጋይና<br>ቀዳሜ ሰማዕት | ፪ 11<br>አቤል ጻድቅ | ፫ 12<br>አባ መጣዕ<br>(ሊባኖስ)<br>ኢትዮጵያዊ |
| ፬ 13<br>ወንጌላዊው ዮሓንስ:<br>ከ፲፪ቱ<br>ሓዋርያት ፩ዱ | ፭ 14 | ፮ 15<br>ኖኅ፤<br>ዕርገተ ኤልያስ | ፯ 16<br>የአስተርእዮ<br>ቅድስት ሥላሴ | ፰ 17 | ፱ 18 | ፲ ከተራ: 19<br>(ለጥምቀት በዓል<br>ዋዜማ: ውኃ:<br>ከወንዝ ተወስዶ<br>የሚከተርበት)፤<br>የጾመ ማርያም<br>ማብቂያ::<br>(ጾመ ገሃድ) |
| ፲፩ 20<br>በዓለ አስተርእዮ<br>ወጥምቀት::<br>ኢትዮጵያዊው<br>ጃንደረባ አቤሜሌክ::<br>በቅዳሴ ጸሎቱ:<br>የጥምቀት ወንዝ<br>የቆመለት: የተጉለቱ<br>ታቦት ዋሻ ካህን:<br>ትልቁ<br>ወልደ ኢየሱስ:: | ፲፪ 21<br>ጌታ:<br>በቃና ዘገሊላ<br>ሠርግ:<br>በቅድስት<br>እናቱ ፈቃድ:<br>የመጀመሪያ<br>ተአምሩን<br>ያሳየበት፤<br>ሊቀ መላእክት<br>ሚካኤል | ፲፫ 22<br>በ፴፬ ዓ.ም.<br>በዘመኗ:<br>በጃንደረባዋ<br>አማካይነት:<br>ክርስትና<br>ወደአገርዋ<br>የመጣላት:<br>ሕንደኬ<br>ንግሥተ<br>ኢትዮጵያ | ፲፬ 23<br>እንበረም: ሊቀ<br>ካህናት ዘአኵስም:<br>በ፫፻፳፭ ዓ.ም.<br>የኢትዮጵያን<br>ሥርዓተ<br>ቤተ ክርስቲያን<br>እንዲሟላ ያደረገ | ፲፭ 24<br>ቂርቆስ:<br>የ፫ ዓመት<br>ሕጻን ሰማዕት | ፲፮ 25<br>ኢየሉጣ ሰማዒት:<br>የሕጻኑ ቂርቆስ<br>እናት | ፲፯ 26 |
| ፲፰ 27 | ፲፱ 28 | ፳ 29 | ፳፩ 30<br>የቅድስት<br>ድንግልማርያም<br>ፍልሰተ ሥጋ፤ | ፳፪ 31 | ፳፫ 1 | ፳፬ 2 |
| ፳፭ 3 | ፳፮ 4 | ፳፯ 5<br>ዕርገተ ሄኖክ | ፳፰ 6 | ፳፱ 7 | ፴ 8 | ማስታወሻ:- |

*ሙሴ: ከግብፅ: በስደት: ወደኢትዮጵያ መጥቶ: ስለኢትዮጵያዊነት: ከኢትዮጵያዊው ካህን: ከዮቶር ተምሮ ካመነ በኋላ: የካህኑን ሴት ልጅ: ሲጳራን አገባ፤ የአማቱን በጎች ሲጠብቅ ሣለም: እነሆ: እግዚአብሔር ተገልጸለት: ያዘዘውን ኹሉ በመፈጸሙ: ኢትዮጵያዊነትን መቀበሉ: እውን ኾኗል:: ከዚህ ኢትዮጵያዊነቱ የተነሣም: የኋላ ኋላ: በወንድሙና በእኅቱ ሳይቀር: ከእሥራኤል ሕዝብ በደል እንደደረሰበት ተጽፏል:: ሙሴና የእሥራኤል ሕዝብ: ገና በምድረ በዳ ሠፍረው ሣሉ: የሚቃጠልንና ሌላ መሥዋዕትን: ለእግዚአብሔር በማቅረብ: ሥርዓተ ክህነትን፥ ስለሕዝብ አስተዳደርና ፍትሕ አሰጣጥም በማስተማር: ሥርዓተ መንግሥትን: አማቱ ዮቶር: ለሙሴና ለአሮን፥ ለሕዝቡ ሹማግሌዎችም ኹሉ ማሳየቱ: በቅዱሳት መጻሕፍት ተመዝግቧል:: ዘጸአ. ፫፥ ፩-፭፤ ፲፰፥ ፩-፳፯:: ዘኁል. ፲፪፥ ፩-፲፭::*

| | |
|---|---|
| የጥር ወር ምንባብ:- | መጽሓፈ ሩትና የማቴዎስ ወንጌል:: |

# ፳፻ ዓመተ ምሕረት ወርኀ የካቲት ዘመነ ዮሐንስ ወንጌላዊ

2000 Era of Mercy. Month of Yekatit (Feb.-Mar., 2008). Year of John the Evangelist

| እሑድ Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ቅዳሜ Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፴ 9<br>ቅድስት | ማስታወሻ:- | | | | | ፩ 9<br>ስለመቅዶንዮስ ኑፋቄ የ፻፶ ሊቃውንት ጉባኤ በቍስጥንጥንያ |
| ፪ 10<br>መርዓዊ፤ | ፫ 11<br>የግሼን ማርያም አምባ፡ በ፲፭፻፴፪ ዓ.ም. በአሕመድ ግራኝ ጦር የተመዘበረበት | ፬ 12<br>ጣይቱ ብጡል፡ ብርሃን ዘኢትዮጵያ | ፭ 13 | ፮ 14<br>ማርያም እንተ ዕፍረት፡ ጌታን በሽቱና በእንባዋ እግሩን ያጠበችው | ፯ 15 | ፰ 16 |
| ፱ 17 | ፲ 18<br>ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ፤<br><br>የጾመ ኢትዮጵያ (ነነዌ) መግቢያ፤ | ፲፩ 19 | ፲፪ 20<br>በ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. የኢትዮጵያውያን ሰማዕታት የግፍ እልቂት፡ በፋሺስት ጣልያን፤<br>የጾመ ኢትዮጵያ ማብቂያ፤ | ፲፫ 21 | ፲፬ 22 | ፲፭ 23 |
| ፲፮ 24<br>**ኪዳነ ምሕረት**<br>በድንግል ማርያም እና በኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘው | ፲፯ 25 | ፲፰ 26<br>አዝማች ደገልሓን የአሕመድ ግራኝን ወራሪ ጦር የተዋጋ ኢትዮጵያዊ ጀግና | ፲፱ 27 | ፳ 28 | ፳፩ 29<br>ከይሁዲቷ ጉዲት አገዛዝ በኋላ፡ በ፱፻፴፫ ዓ. ም. በአገዉ (በዘአጌው) መርሓ ተክለ ሃይማኖት፡ ኢትዮጵያዊው የመልከ ጼዴቅ ሥርዓተ መንግሥት የተመለሰበት | ፳፪ 1 |
| ፳፫ 2<br>ኢትዮጵያ፡ ኃይሏ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ መኾኑ የተረጋገጠበት የአድዋ ድል::<br>ዘወረደ (ቅበላ) | ፳፬ 3<br><br>የጾመ ሕርቃልና የዓቢይ ጾም መግቢያ፤ | ፳፭ 4 | ፳፮ 5 | ፳፯ 6<br>አሕመድ ግራኝ በ፲፭፻፴፭ ዓ.ም. ድል የተመታበት | ፳፰ 7 | ፳፱ 8 |

*"ይሁዳ፡ የአንበሳ ደቦል ነው፤ ያስነሣውስ ዘንድ ማን ይችላል? ገዥ የኾነው እስኪመጣ ድረስ፡ በትረ መንግሥት ከይሁዳ፥ የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል አይጠፋም:: የአሕዛብም መታዘዝ ለእርሱ ይኾናል::" "በዙፋኑም ላይ በተቀመጠው፡ በቀኝ እጁ ያለውን መጽሓፍ ሊዘረጋ ወይም ሊመለከተው የሚገባው ማንም ስላልተገኘ፡ እጅግ አለቀስሁ፤ ከሃያ አራቱ አለቆች አንዱ፡ 'ኢትብኪ! ናሁ ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ'፡ ማለትም፡ 'አታልቅስ! እነሆ፥ ከይሁዳ ነገድ የኾነው አንበሳ፡ እርሱም የዳዊት ሥር፡ መጽሓፉን ይዘረጋ ዘንድ፥ ሰባቱንም ማኅተም ይፈታ ዘንድ ድል ነሥቷል!' አለ፤" የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል፡ ኢትዮጵያውያን በሃይማኖት ተቀብለው፡ በምግባር ስለፈጸሙት፡ እውነተኞቹ እስራኤል፡ እነርሱ መኾናቸው ተረጋግጧል::* ዘፍጥ. ፵፱፥ ፱-፲፤ ራእ. ፭፥ ፩-፭::

| | |
|---|---|
| የየካቲት ወር ምንባብ:- | ኦሪት ዘዳግም፥ ትንቢተ ዮናስና የማርቆስ ወንጌል:: |

# ፳፻ ዓመተ ምሕረት ወርኀ መጋቢት ዘመነ ዮሐንስ ወንጌላዊ

2000 Era of Mercy. Month of Megabit (Mar.-Apr., 2008). Year of John the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የካቲት<br>፴ 9<br>ቅድስት፤ | ፩ 10<br>አጼ ዮሓንስ ፬ኛ፡ የመተማው ሰማዕት በእስላም ወራሪ የተሠየፈ።<br>የጌታ የ፵ ቀን ጾም መነሻ፤ | ፪ 11 | ፫ 12 | ፬ 13 | ፭ 14<br>ገብረ መንፈስ ቅዱስ | ፮ 15 |
| ፯ 16<br>ምኲራብ፤ | ፰ 17<br>ማትያስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ | ፱ 18 | ፲ 19 | ፲፩ 20<br>አባ አሌፍ፡ ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ | ፲፪ 21 | ፲፫ 22 |
| ፲፬ 23<br>መጻጉዕ፤ | ፲፭ 24 | ፲፮ 25 | ፲፯ 26 | ፲፰ 27 | ፲፱ 28 | ፳ 29 |
| ፳፩ 30<br>ደብረ ዘይት፤ | ፳፪ 31 | ፳፫ 1<br>ዳንኤል ነቢይ | ፳፬ 2<br>ንግሥት ዘውዲቱ ምኒልክ | ፳፭ 3<br>የበጋ ወራት ማብቂያ | ፳፮ 4<br>የበልግ ወራት መግቢያ | ፳፯ 5<br>አጼ ገላውዴዎስ፡ ካቶሊካውያንን የተቋቋመና በእስላም ወራሪ ሰማዕትነትን የተቀበለ |
| ፳፰ 6<br>ገብር ኄር፤ ቈስጠንጢኖስ ንጉሥ፡ ስለሃይማኖትና ስለፍትሓ ነገሥት ዝግጅት፡ የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ጉባኤን በኒቅያ ያሰባሰበ። | ፳፱ 7 | ፴ 8 | ማስታወሻ፡- | | | |

*"እነሆ፥ ለዳዊት፡ ጻድቅ ቊጥቋጥ የማስነሣበት ዘመን ይመጣል። እርሱም እንደንጉሥ ይነግሣል፤ ይከናወንለታልም፤ በምድርም፡ ፍርድንና ጽድቅን ያደርጋል። ...በዘመኑ እውነት ታብባለች፤ ሰላምም ይበዛል። ከባሕር እስከባሕር ድረስ፥ ከወንዝም እስከምድር ዳርቻ ድረስ ይገዛል። በፊቱም ኢትዮጵያውያን ይሰግዳሉ። ጠላቶቹም አፈር ይልሳሉ።"... "እግዚአብሔር ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው፤ በምድርም መካከል መድኃኒትን አደረገ። አንተ፡ የእባቦችን ራስ፡ በውኃ ውስጥ ሰበርህ! የዘንዶውንም ራሶች ቀጠቀጥህ! ለኢትዮጵያ ሰዎችም ምግባቸውን ሰጠሃቸው!"*

ኤር. ፳፫፥ ፭-፮፤ መዝ. ፸፩፥ ፯-፱፤ ፸፫፥ ፲፪-፲፬።

| | |
|---|---|
| የመጋቢት ወር ምንባብ፡- | ትንቢተ ኢሳይያስ እና የዮሐንስ ወንጌል። |

# ፳፻ ዓመተ ምሕረት ወርኀ ሚያዝያ ዘመነ ዮሐንስ ወንጌላዊ

2000 Era of Mercy. Month of Miazia (Apr.-May, 2008). Year of John the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | ፩ 9 | ፪ 10 | ፫ 11 | ፬ 12 |
| ፭ 13<br>ኒቆዲሞስ<br>ሕዝቅኤል ነቢይ | ፮ 14<br>አርበኛው መሪ ጻግማዊ<br>አጼ ቴዎድሮስ | ፯ 15<br>ኢያቄም:<br>የድንግል<br>ማርያም አባት | ፰ 16 | ፱ 17 | ፲ 18 | ፲፩ 19 |
| ፲፪ 20<br>ሆሣዕና<br>ደብረ ብርሃን በ፲፭፻፳፫ ዓ. ም በአሕመድ ግራኝ የተቃጠለበት | ፲፫ 21<br>በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. ፋሺስት ጣልያን ማኅበረ ሥላሴን: በአየር ኃይሉ የደበደበበት፤ የሰሙነ ሕማማት መግቢያ:: | ፲፬ 22 | ፲፭ 23<br>በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. ሦስት የማኅበረ ሥላሴ ገዳም መነኰሳት: በፋሺስት ጣልያን ጦር የተሠዉበት | ፲፮ 24<br>ጸሎተ ሓሙስ፤ | ፲፯ 25<br>ስቅለት<br>ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ | ፲፰ 26<br>ጌታ በመቃብር ያረፈባት: ቀዳሚት ሰንበት፤ |
| ፲፱ 27<br>በዓለ ትንሣኤ ፋሲካ | ፳ 28<br>ማዕዶት:<br>(በሕይወተ ሥጋ እያሉ በመንፈስ: ወደትንሣኤ ሕይወት መሻገር::) | ፳፩ 29<br>እጨጌ ዕንባቆም: ሰባኬ ሃይማኖትና ሓዋርያ | ፳፪ 30 | ፳፫ 1<br>አዳም ሓሙስ<br>(የ፭ሺ፭፻ው ዓመት ተስፋ ፍጻሜ ዝክር)<br>ጊዮርጊስ ሰማዕት | ፳፬ 2 | ፳፭ 3 |
| ፳፮ 4<br>ዳግም ትንሣኤ፤<br>(ከፊተኛው የመንፈስ ትንሣኤ በኋላ ያለው የመጨረሻ ትንሣኤ መታሰቢያ::) | ፳፯ 5<br>ኢትዮጵያ: በፋሺስት ጣልያን ላይ በተቀዳጀችው ድል: ነጻነቷ የሚጠበቀው: በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ መኾኑ የተረጋገጠበት | ፳፰ 6 | ፳፱ 7 | ፴ 8<br>ማርቆስ ወንጌላዊ | ማስታወሻ:- | |

*የሳባ ንግሥት: በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን: የሰሎሞንን: ዝናውን በሰማች ጊዜ: ስለሃይማኖቱና ስለእውነተኛ ማንነቱ: በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ: ከታላቅ ጓዝ ጋር ከአገርዋ ከኢትዮጵያ ተነሥታ: ወደኢየሩሳሌም መጣች:: ለንጉሡም: መቶ ሃያ መክሊተ ወርቅ፥ እጅግም ብዙ ሽቱ፥ የከበረም ዕንቍ ሰጠችው፤ የሳባ ንግሥት: የሰጠችውን የመሰለ የስጦታ ብዛት: ከዚያ ወዲያ አልመጣም:: የትንቢቱ ፍጻሜና ዘላለማዊው ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ: ከእርሱ ምልክትን ለሚጠይቅ: ከሃዲና ዓመፀኛ፥ ዘማዊም ትውልድ: እንዲህ የሚል: የመጨረሻ መልስን ሰጠ:- ንግሥተ ዓዜብ (ኢትዮጵያ): በፍርድ ቀን: ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፋረዳለች፥ ታሳፍረዋለችም፤ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት: ከምድር ዳር መጥታለችና፤ እነሆም: ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ! ከዚህ ፍርድ ለመዳን: እጆቿን ወደእግዚአብሔር ዘርግታ ከምትኖረው: ከኢትዮጵያ ጋር: የምድር መንግሥታት መሪዎች ኹሉ: ለእግዚአብሔር ተቀኙ! ዘምሩም!*
፩ኛ ነገ. ፲፥ ፩-፲፤ ማቴ. ፲፪፥ ፵፪፤ መዝ. ፷፯፥ ፴፩-፴፪::

| የሚያዝያ ወር ምንባብ:- | ትንቢተ ዳንኤልና የጳውሎስ መልእክታት:: |
|---|---|

# ፳፻ ዓመተ ምሕረት ወርኀ ግንቦት ዘመነ ዮሐንስ ወንጌላዊ

2000 Era of Mercy. Month of G'nbot (May-June, 2008). Year of John the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | | | ፩ 9<br>ቅድስት ድንግል ማርያም በሊባኖስ ተራራ የመወለዷ መታሰቢያ | ፪ 10<br>ኢዮብ ጻድቅ: ኢትዮጵያዊ |
| ፫ 11 | ፬ 12 | ፭ 13<br>ኢትዮጵያውያኑ ኤርምያስ ነቢይ፥ ደቀ መዛሙርቱ አቤሜሌክ እና ባሮክ | ፮ 14<br>የደብረ ሊባኖሷ ቅድስት ሰሎሜ ኢትዮጵያዊት | ፯ 15 | ፰ 16 | ፱ 17<br>ዕሌኒ ንግሥት: የጌታን መስቀል አስቆፍራ ያስገኘች |
| ፲ 18<br>በሃይማኖታቸው ጽናት ከባቢሎን እሳት የዳኑት አናንያ፥ አዛርያና ሚሳኤል: | ፲፩ 19<br>ያሬድ: ኢትዮጵያዊው ማኅሌታይ ካህን፤ አባ አሴር: የባሌ መምህር | ፲፪ 20<br>አጼ እስክንድር: የእስላምን ወራሪ ጦር ሲከላከል: ሰማዕትነትን: በወጣትነቱ የተቀበለ፤ ዮሐንስ አፈወርቅ | ፲፫ 21<br>ርክበ ካህናት፤<br>የደብረ ሊባኖስ ገዳም መነኰሳት በ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር የተሠዉበት | ፲፬ 22 | ፲፭ 23<br>ናትናኤል: ከ፲፪ቱ ሐዋርያት ፩ዱ | ፲፮ 24 |
| ፲፯ 25 | ፲፰ 26 | ፲፱ 27<br>ኢትዮጵያዊው አቡነ እግዚእ | ፳ 28<br>ቅዱስ አጼ ካሌብ: ወደናግራን (የመን) ግዛቱ: በመርከብ ዘምቶ: አይሁዳዊዉን ወራሪ ጠላት: ድል ያደረገው | ፳፩ 29<br>የደርግ የክህደት አገዛዝ በ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. የተወገደበት | ፳፪ 30 | ፳፫ 31 |
| ፳፬ 1<br>ዕንባቆም ነቢይ | ፳፭ 2<br>ቅድስት ሰሎሜ: በሕፃኑ ኢየሱስና እናቱ ስደት ያልተለየች | ፳፮ 3<br>ቶማስ: ከ፲፪ቱ ሐዋርያት ፩ዱ | ፳፯ 4 | ፳፰ 5<br>ዕርገት | ፳፱ 6<br>አባ አፍጼ፤ አባ ጉባ: ከ፱ኙ ቅዱሳን ፱ቱ | ፴ 7 |

*ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደመቅደስ ወጥቶ ሲያስተምር: ሊገድሉት ለሚፈልጉት አይሁድ: "ቅን ፍርድን ፍረዱ እንጂ: መልክን አይታችሁ አትፍረዱ!" አላቸው:: ለምን እንዲህ አላቸው? "መልክን አይታችሁ አትፍረዱ!" የሚለው የጌታ ቃል: ቀድሞ: በሙሴ ላይ የተነሣሣባቸው ቅንዓት የተከሠተው: በኢትዮጵያዊት ሚስቱ ምክንያት እንደነበረ ኹሉ: አሁን ደግሞ በእርሱ: በኢየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያዊነት ላይ የተቀጣጠለ መኾኑን ሲያመለክታቸው እንደኾነ ማስተዋል ነው:: "'የእስራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ: ለእኔ: እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?' ይላል እግዚአብሔር"* ሲል: ነቢዩ አሞጽ የተናገራቸውን ቃል: በዚያን ጊዜም አላስተዋሉትም::

ዮሐ ፯፥ ፲፬-፳፬፤ ዘኍል. ፲፪፥ ፩-፲፮፤ አሞ. ፱፥ ፯::

| | |
|---|---|
| የግንቦት ወር ምንባብ:- | መጻሕፍት አስቴር፥ ምሳሌና መክብብ:: |

# ፳፻ ዓመተ ምሕረት ወርኀ ሰኔ ዘመነ ዮሐንስ ወንጌላዊ

2000 Era of Mercy. Month of Seney (June-July, 2008). Year of John the Evangelist

| እሑድ Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ቅዳሜ Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 8<br>ወንድሞቹ የሸጡት የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍ እና ካማዊት ሚስቱ አስናት | ፪ 9 | ፫ 10 | ፬ 11 | ፭ 12 | ፮ 13<br>በፋሺስት ጣልያን የተመራ የራያ እስላም፡ በ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. የሸዋ ቆላ ኢትዮጵያውያንን በሰለባ የፈጀበት | ፯ 14 |
| ፰ በዓለ ፰<br>**በዓለ መንፈስ ቅዱስ** 15 | ፱ 16<br>ሳሙኤል ነቢይ<br>የጾመ ሓዋርያት መግቢያ፤ | ፲ 17 | ፲፩ 18<br>ጾመ ድኅነት፡- የረቡዕና ዓርብ ጾም መነሻ | ፲፪ 19<br>ሚካኤል ሊቀ መላእክት<br>አጼ ላልይበላ (ላሊበላ) | ፲፫ 20 | ፲፬ 21 |
| ፲፭ 22 | ፲፮ 23 | ፲፯ 24<br>አባ ገሪማ፡ ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ | ፲፰ 25 | ፲፱ 26 | ፳ ሕንጸታ፡ 27<br>በአጻምና ሔዋን ኪዳነ ልቦና፡ ኢትዮጵያ የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ኪዳነ ምሕረት፡ ኢየሩሳሌም ተፈጸመች፡ ኤልሳዕ ነቢይ | ፳፩ 28<br>በቅዱሱ ኪዳን ላይ ክህደትና ዓመፅ የፈጸመውን የኢትዮጵያ ትውልድ ሊቀጣ የተላከው ግፈኛው ደርግ በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም. የተቋቋመበት |
| ፳፪ 29 | ፳፫ 30<br>ንጉሥ ሰሎሞን የምኒልክ አባት | ፳፬ 1<br>ኢትዮጵያዊው ሙሴ (ጸሊም) | ፳፭ 2<br>ያስቆሮቱ ያይደለ፡ ሓዋርያው ይሁዳ፡ የጌታ የቅርብ ዘመድ፤ የበልግ ወራት ማብቂያ | ፳፮ 3<br>ኢያሱ ወልደ ነዌ፤<br>የክረምት ወራት መግቢያ | ፳፯ 4 | ፳፰ 5 |
| ፳፱ 6<br>በሺ፬፻፬ ዓ.ም. የተቀባው ስመ ጥሩው ጻድቅ ቀዳማዊ አጼ ቴዎድሮስ | ፴ 7<br>የላስታ ላልይበላ (ላሊበላ) አብያተ ክርስቲያን፡ በ፲፭፻፳፭ ዓ.ም. በአሕመድ ግራኝ ጦር የተበዘበዙበት | ማስታወሻ፡- | | | | |

*“የእግዚአብሔር መልአክ፡ ፊልጶስን፡- 'ተነሥተህ በደቡብ በኩል፡ ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው፡ የምድረ በዳ መንገድ ኺድ!' አለው:: ተነሥቶም ኼደ:: እነሆም፡ ሕንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ፥ በገንዘቧም ኹሉ የሠለጠነ፡ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር:: ሲመለስም፡ መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን፡ 'ወደዚህ ሠረገላ ቅረብና ተገናኝ!' አለው:: የአዲስ ኪዳኑ አቤሜሌክ የኾነው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም፡ ወዲያው፡ 'ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ!' ስላለ፡ አጠመቀው:: ከውኃው ከወጡ በኋላ፡ አቤሜሌክ፡ በተደረገለት ዕፁብ ድንቅ መለኮታዊ የቸርነት ሥራ፥ በተቀዳጀውም ዘለዓለማዊ የመንፈስ ቅዱስ ብፅዕና፡ እጅግ ተደንቆና ደስ ብሎት ስለነበረ፡ ፊልጶስ፡ ካጠገቡ፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የመነጠቁን ተአምር ሳያስተውል፡ ዝም ብሎ፡ የሠረገላ መንገዱን ቀጠለ::* የሐዋ. ፰፥ ፳፮-፴፱::

| የሰኔ ወር ምንባብ፡- | የሓዋርያት ሥራና ንዑሳኑ መልእክታት:: |
|---|---|

# ፳፻ ዓመተ ምሕረት ወርኀ ሐምሌ ዘመነ ዮሐንስ ወንጌላዊ

2000 Era of Mercy. Month of Hamley (July-Aug., 2008). Year of John the Evangelist

| እሑድ Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ቅዳሜ Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | ፩ 8 | ፪ 9 ታዴዎስ: ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ | ፫ 10 | ፬ 11 የጾመ ሓዋርያት ማብቂያ፤ | ፭ 12 ቅዱሳን ሓዋርያት ጴጥሮስ ወጳውሎስ |
| ፮ 13 ዕርገተ እዝራ | ፯ ሥሉስ ቅዱስ: 14 በአብርሃም ቤት የተገኙበት፤ በ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር በሰማዕትነት የተሠዉት ፳፰ቱ የደብረ ሊባኖስ መነኰሳት | ፰ 15 | ፱ 16 | ፲ 17 | ፲፩ 18 | ፲፪ 19 |
| ፲፫ 20 | ፲፬ 21 | ፲፭ 22 ኤፍሬም ሶርያዊ የውዳሴ ማርያም ደራሲ | ፲፮ 23 | ፲፯ 24 እጨጌ እንድርያስ: በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የነበረ፤ ነቢዩ ዮናስ ነነዌ የገባበት | ፲፰ 25 ያዕቆብ: የጌታ የቅርብ ዘመድና በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን የመጀ መሪያው ሊቀ ካህናትና ሰማዕት፤ ኢትዮጵያውያኑ ጦብያና ጦቢት | ፲፱ 26 ሊቀ መላእክት ገብርኤል: ሰማዕቱ ቂርቆስን እና እናቱ ኢየሉጣን ከሚነድድባቸው እሳት ያዳነበት |
| ፳ 27 | ፳፩ 28 አጼ ሠርፀ ድንግል: ሃይማኖታዊው ተጋዳይ | ፳፪ 29 ዑራኤል ሊቀ መላእክት | ፳፫ 30 ቅዱስ ጴጥሮስ÷ ኢትዮጵያዊው ሰማዕት በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር የተሠየፈው | ፳፬ 31 የደብረ ሊባኖስ ገዳም በ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. በአሕመድ ግራኝ የተቃጠለበት÷ መነኮሳቱም: ራሳቸውን በሰማዕትነት: በእሳቱ የማገዱበት | ፳፭ 1 አባ ሕፃን ሞአ ኢትዮጵያዊ | ፳፮ 2 ጻድቅ ዮሴፍ ኢትዮጵያዊ: ሕፃኑን ኢየሱስና እናቱን ለማገልገል በፈጣሪ የተመረጠ |
| ፳፯ 3 | ፳፰ 4 | ፳፱ 5 | ፴ 6 ማርያም ክብራ: (እቴጌ ናዖድ ሞገሳ) የአጼ ናዖድ ሚስት | ማስታወሻ:- | | |

*እንግዴህ አይሁድ: "ከሰማይ የወረደ እንጀራ እኔ ነኝ!" ስላለ: ስለኢየሱስ አንጐራጐሩ፤ "ይህ ሰው: ሥጋውን ልንበላ÷ ደሙንም ልንጠጣ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል?" ብለውም ተከራከሩ:: ከዚህ የተነሣ: ከደቀ መዛሙርቱ ሳይቀር: "ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው፤ ማን ሊሰማው ይችላል?" ብለው ብዙዎቹ ወደኋላቸው ተመለሱ::* በዚህ ጊዜ: ጌታችን *ኢየሱስ ክርስቶስ "እውነት÷ እውነት እላችኋለሁ! ሥጋዬን ካልበላችሁ÷ ደሜንም ካልጠጣችሁ: በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም፤ ሥጋዬን የሚበላ÷ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤ እኔም: በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ::"* ሲል: ሊድን ለሚፈልግ: ለዓለሙ ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ: የመጨረሻ አዋጅ የኾነውን የእግዚአብሔርን እውነት ገልጦና አስረግጦ ተናገረ:: ዮሐ.፮÷ ፶፩-፶፱::

| | |
|---|---|
| **የሓምሌ ወር ምንባብ:-** | **ደቂቀ ነቢያት እና ራእየ ዮሓንስ::** |

# ፳፻ ዓመተ ምሕረት ወርኀ ነሐሴ ዘመነ ዮሐንስ ወንጌላዊ

2000 Era of Mercy. Month of Nehassey (Aug.-Sept., 2008). Year of John the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ጳጉሜ | | ጳጉሜ | | | | |
| ፪ 7 | ፫ ሩፋኤል 8<br>ሊቀ መላእክት፤ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ፡ | ፬ 9<br>የቅዱሳን ኹሉ መታሰቢያ | ፭ 10<br>የንስሓ ጾም ማብቂያ፤<br>ዓሞጽ ነቢይ | ፩ የፍልሰታ 7<br>ለማርያም ጾምና ሱባዔ መግቢያ፤ ጌታን የገነዙት ዮሴፍና ኒቆዲሞስ | ፪ 8 | ፫ 9 |
| ፬ 10 | ፭ 11<br>አባ ፊልጶስ ዘደብረ ቢዘን | ፮ ማርያም 12<br>መግደላዊት፡ የጌታን ትንሣኤ ቀድማ አይታ ያበሠረች | ፯ 13<br>አጼ ናዖድ፡ የመልክዓ ማርያም እና መልክዓ ኢየሱስ ደራሲ | ፰ 14 | ፱ 15 | ፲ 16 |
| ፲፩ 17 | ፲፪ 18 | ፲፫ 19<br>ጌታ፡ በግርማ መለኮቱ የታየ በት ደብረ ታቦር። ቡሔ | ፲፬ 20 | ፲፭ 21<br>የፍልሰታ ለማርያም ጾምና ሱባዔ ማብቂያ፤ | ፲፮ 22<br>**የቅድስት ድንግል ማርያም በዓለ ትንሣኤ** | ፲፯ 23 |
| ፲፰ 24<br>አዝማች አዳሉ፡ የአሕመድ ግራኝን ወረራ በጀግንነት ተቋቁሞ የተሠዋ | ፲፱ 25 | ፳ 26 | ፳፩ 27 | ፳፪ 28 | ፳፫ 29<br>አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፡ ኢትዮጵያዊ፡ የመዓዛ ቅዳሴና የሰዓታት ጸሎታት ደራሲ | ፳፬ 30<br>በ፲፪ኛው ፻ ዓመት ኢትዮጵያዊዉ ሥርዓተ መንግሥት በሰላም እንዲቀጥል ያስማማ፡ እጨጌ ተክለ ሃይማኖት፤ ክርስቶስ ሠምራ ኢትዮጵያዊት |
| ፳፭ 31 | ፳፮ 1 | ፳፯ 2<br>እጨጌ ፊልጶስ፤ ታላቁ ሓዋርያና አጼ ዓምደ ጽዮን፡ ንስሓ እንዲገባ በግልጽ በመገሠጹ ጽኑ መከራን የተቀበለ | ፳፰ 3<br>አብርሃም፥ ይስሓቅና ያዕቆብ | ፳፱ 4<br>ንዋየ ክርስቶስ (አለቃ ዘካርያስ) እስላሞችን፡ በሃይ ማኖት ጉባኤ የረ ታና ብዙዎቹን ወደክርስትና የመ ለሰ ኢትዮጵያዊ ሓዋርያ፥ የኢትዮ ጵያዊነት አብነትና ድልድይ የኾነ | ፴ 5<br>ኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ፡ እርሱም ቅዱሱን ኪዳን፡ ከኖኅ የተረከበው ቀዳማዊው፡ አብርሃምን በባረከው በማዕከላዊው አማካይ ነት፡ ለደኃራዊውና ለአ ማናዊው መልከ ጼዴቅ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቀዳሚ አርአያ የኾነው | ጳጉሜ<br>፩ 6<br>የንስሓ ጾም መግቢያ |

*መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል፡ ድንግል ማርያምን፡ "ደስ ይበልሽ! ጸጋ የሞላብሽ ሆይ! እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው! አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ!" አላት፡፡ መንፈስ ቅዱስ የሞላባት ኤልሣቤጥም፡ "አንቺ፡ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ! የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው!" አለች፡፡*

*ቅድስት ድንግልም፡ "ነፍሴ፡ እግዚአብሔርን፡ እጅግ ታልቀዋለች፤ መንፈሴም፡ በአምላኬና በመድኃኒቴ፡ ሐሤት ታደርጋለች፤ የባሪያውን መከራዋን ተመልክቷልና፡፡ እነሆ፡ ከዛሬ ጀምሮ፡ ትውልድ ኹሉ 'ብፅዕት' ይሉኛል፤ ብርቱ የኾነ እርሱ፡ በእኔ፡ ታላቅ ሥራን አድርጓልና!" አለች፡፡ ሉቃ. ፩፥ ፳፰-፶፡፡*

| | |
|---|---|
| የነሓሴና የጳጉሜ ወራት ምንባብ፡- | ትንቢተ ሕዝቅኤል፥ መጽሓፈ ጦቢትና የሉቃስ ወንጌል፡፡ |